# በቶሮንቶ ኢትዮጵያውያን
# በኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞችን ጉዳይ አስመልክቶ
# የወጣ የጋራ አቋም መግለጫ

ዛሬ ታሕሣሥ 26 ቀን 2001 ዓ.ም በ 427 ብሉር ስትሪት ዌስት በሚገኘው አዳራሽ፤ በወያኔ የግፍ ሰለባ በሆኑት በእነ አርቲስት ቲዎድሮስ ካሣሁን እና በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ የፖለቲካ እስረኞችን ጉዳይ በተመለከተ ተቋርቋሪ ኢትዮጵያውያን በቶሮንቶ አስተባባሪ ኮሚቴ፣ በጠራው ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ የተገኘን እኛ በቶሮንቶ ነዋሪ የሆንን ኢትዮጵያውያን፤

ሀ. የኢትዮጵያን ብርቅዬ ምሁራንን፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችን፣ የፖለቲካ መሪዎችንና አባሎችን፣ ጋዜጠኞችን፣ የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪዎችን፣ የሃይማኖት አባቶችን፣ ህጻን፣ ወጣት፣ አዛውንት ዜጎችን በወያኔ አገዛዝ በእስር ተሰቃይተውና በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድለው የሕይወት መስዋዕትነት የከፈሉትን ውድ ኢትዮጵያውያንን፤

ለ. በወያኔ የጎሳ ፓለቲካ ፖሊሲ ለዘመናት በሰላም የኖረውን ሕዝብ አንዱን በሌላው ላይ በመቀስቀስና ግጭት በመፍጠር በአርሲ፣በበደኖ፣በሀረር፣በአርባጉጉ፣ በባሌ፣ በጋምቤላ፣ በአዋሳ፣በቦረና እንዲሁም በተለያዩ ጊዜና ቦታዎች በ10 ሺዎች የሚቆጠሩ ላለቁት ወገኖቻችን፤ እንዲሁም የወያኔን አገዛዝ ሲታገሉ በየጊዜው ለተሰዉትና በምርጫ 97 ሳቢያ የተጨፈጨፉትን ወገኖቻችን፡ የታሰሩና የተሰደዱትን ኢትዮጵያውያንን፤

ሐ. እንዲሁም በቅርቡ የመለስ አገዛዝ የግፍ ፍርድ ሰለባ የሆነውን አርቲስት ቲዎድሮስ ካሣሁንና በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞችን ሻማ በማብራትና በህሊና ጸሎት አስበናቸዋል፡፡

አያይዘንም በአጠቃላይ በሀገራችን የመለስ ዜናዊ የዘረኝነትና የአምባገነን አገዛዝ በማካሄድ ላይ ስላለው መጠነ ሰፊና የከፋ የሰብዓዊ መብት ረገጣ በተመለከተ ውይይት አካሂደን የሚከተለውን የጋራ መግለጫ አውጥተናል፡፡

1. ስለ ሀገር ፍቅር፣ ስለ ኢትዮጵያዊነት፣ በፍቅርና በህብረት በአንድነት ስለ መኖር በሙያው በማዜምና በመግለጽ ሲያገለግል የነበረው ተወዳጁ አርቲስት ቲዎድሮስ ካሣሁን በወያኔ የተቀነባበረ የሀሰት ውንጀላና የግፍ ፍርድ ባልሰራው ወንጀልና በቂ ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ "ሰውን በመኪና ገድሎ ህይወት አጥፍቷል" በማለት የ 6 ዓመት ጽኑ እስራት ፍርድና የ18 ሺህ ብር መቀጫ እንዲከፍል በወያኔ ካድሬ ዳኛ ተፈርዶበት በቃሊቲ እስር ቤት መጣሉን እናወግዛለን፤ አርቲስት ቲዎድሮስ ካሣሁን የተወነጀለው ስለ ሀገሩና ሕዝቡ ፍቅር ሀሳቡን በመግለጹ ስለ ሆነ የፖለቲካ እስረኛ እንጂ ወንጀለኛ አይደለም፡፡ ስለሆነም በአስቸኳይ እንዲፈታ እንጠይቃለን፡፡

2. በኢትዮጵያ ሰላምን ለማስፈን በማሰብ በተጠራ ጉባኤ ላይ ለመገኘት ሄዶ፣ የመለስ ዜናዊ አምባገነን አገዛዝ 12 ዓመት ያህል ያለ ፍርድ አስሮ ከፈታው በኋላ መልሶ 25 ዓመት ፈርዶ በእስር ቤት የሚማቅቀውን አቶ አበራ የማነአብን፣ ወያኔ ሥልጣም ከያዘ ጀምሮ በደደቢትና በሌሎችም የጉድጓድ እስር ቤቶች ደብቆ ያሰራቸውን፣ በቃሊቲ፣ በዝዋይና በየክፍለሀገሩ አስሮ የሚያሰቃያቸውን፣ በቅርቡ መልሶ ያሰራትን ወት ብርቱካን ሚዲቅሳና ሌሎች የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ በአስቸኳይ እንዲፈታ እንጠይቃለን፡፡

3. ወያኔ ኢትዮጵያን መቆጣጠር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ የት እንዳደረሳችው የማይታወቁት እነ ጺጋዬ ገብረመድህን፣ አበራሽ በርታ፣ ጋዜጠኛ ብርሃኑ እጅጉ እና ሌሎችም ጓዶቻቸውን ሁሉ የት እንዳደረሳቸው እንዲያሳውቅና እንዲፈታቸው እንጠይቃለን። ወያኔ የፖለቲካ ስደተኞችን ከጎረቤት አገሮች እያፈነ መውሰዱ ከፍተኛ የውንብድና ተግባር በመሆኑ እናወግዛለን። በዚህ ዓይነት አፍኖ ከሱዳን ከወሰዳቸው መካከል እነ አጣናው ዋሴና ሌሎችም በአስቸኳይ እንዲፈታ እንጠይቃለን።

4. በፖለቲካ አመለካከታቸውና የተቃዋሚ ድርጅቶች አባል በመሆናቸው ከስራ የማባረር፣ የመደብደብ፣ ንብረታቸው ላይ ጥፋት የማድረስ፣ የማስፈራራት እና ሌሎችም የሰብዓዊ መብቶች መጣስ እየደረሰባቸውና አሁንም እየባሰ በመሄዱ ድርጊቱን እናወግዛለን። የአገሩ መሬት ለሱዳን መሰጠት ያንገበገበው አርቲስት ፋሲል ደሞዝ መቆርቆሩን በማዜሙ የደረሰበትን እስራትና ድብደባ እናወግዛለን። በሌሎችም ዜጎች ላይ ተመሳሳይ ኢ ሰብዓዊ ድርጊት መፈጸሙን እየተቃወምን የሁሉም ዜጎች ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ እንጠይቃለን።

5. ወያኔ ለውጭ ባለሀብቶችና ለደጋፊዎቹ ለአበባና ሌላም ምርት እያለ የተቀነባበረና መጠነ ሰፊ የአርሶ አደሮችን መሬት የመቀማትና ከኑሮአቸው የማፈናቀል ድርጊት በአስቸኳይ እንዲቆም እንጠይቃለን። ከተወለዱበትና ከኖሩበት አካባቢ እየተፈናቀሉና እየተባረሩ የሚያርሱት መሬታቸውና ንብረታቸው ለውጭ አገር ሰዎች እየተሰጠ በገዛ አገራቸው እንደ ባዳ የሚሰቃዩት ኢትዮጵያውያን ወደ ቀድሞው የመኖሪያ ቦታቸው ተመልሰው በሰላም የመኖርና የመስራት መብታቸው እንዲጠበቅ እንጠይቃለን።

6. ኢትዮጵያ ከሱዳን ጋር የሚያዋስናት በብዙ ሺህ ኪሎ ሜትር የሚቆጠር አካባቢ ወያኔ የኢትዮጵያን ለምና የእርሻ  መሬትን በህገወጥና በማንአለብኝነት ለሱዳን በመስጠቱ የተፈናቀሉት ወገኖቻችን መልሰው እንዲቋቋሙ፤ ይንን ለም መሬት ለሱዳን አሳልፎ መስጠት ሕዝቡና የፖለቲካ ድርጅቶች እንዳይቀበሉትና ለአገራቸው መሬትና ለመብታቸው መከበር እንዲታገሉ ጥሪ እናቀርባለን።

7. ለሰብዓዊ መብት መከበርና ለዲሞክራሲ መስፈን በሚታገሉት የፖለቲካ ድርጅቶችና በነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞች ላይ የሚደርሰው ማዋከብና አፈና እንግልትና ስቃይ በአስቸኳይ እንዲቆም እንጠይቃለን።

8. አገራችንን ከወያኔ የዘረኝነትና የአምባገነን አገዛዝ ለማላቀቅ በአገር ቤትም ሆነ በውጭ የሚካሄደው ትግል አጋር ሆነን በሚቻለው መንገድ ሁሉ ለመርዳት፣ ትግሉንም በጽናትና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ቆርጠን ለመታገል ያለንን ጽኑ አቋም ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንገልጻለን።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!
ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆችዋ ታፍራ ተከብራ ትኖራለች!

ታህሣሥ 26 ቀን 2001 ዓ.ም
ቶሮንቶ፤ ካናዳ